በቤ/ጉ/ክ/መ/የዋናው ኦዲተር መ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ

መግቢያ

<u>የቤ/ጉ/ክ/መ/የዋና ኦዲተር መ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት የሥራ ዕቅድ</u>

የቤ/ጉ/ክ/መንግስት ዋና ኦዲተር መ/ቤት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ ቁጥር 167/2011 መሰረት የኦዲት ስርዓትን ለማጠናከር የክልሉን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ በማግኘት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ፣ በልዩ ልዩ የልማትና አስተዳደር መስኮች የተሠማሩ የመንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የገንዘብ አስተዳደር፣ ተገቢውን የሂሳብ አያያዝ ስርዓት የተከተለ፣ የገቢ አሰባሰባቸው፣የወጪ አፈቃቀዳቸው፣ የበጀትና የንብረት አስተዳደራቸው የመንግሥት ህጎችን፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑን እንዲሁም ዕቅዳቸው በቅልጥፍናና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በማከናወን የሚጠበቅባቸውን ግብ ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እንዲሁም በክልሉ መንግስት አወቃቀር ሥር በሚገኙ መ/ቤቶች ውስጥ የአሠራር ግልፅኝነት፣ውጤታማነት እና የፋይናንስ ተጠያቂነት ለማስፈን ኦዲት ዋነኛ መሣሪያ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህንን በአዋጅ የተሠጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት መ/ቤታችን በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በ142 የሰው ኃይል የተጠና ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ዋና ኦዲተር፣ ም/ዋና ኦዲተር፣ 9 ዳይሬክቶሬቶች፣አንድ የሥነ ምግባር መኮንን፣ 50 የተለያዩ ባለሙያዎች እና 33 ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች በአጠቃላይ በ95 (ዘጠና አምስት) የሰው ኃይል ያሉት ሲሆን በ2018 በጀትም በዋና የሥራ ሂደቶች ላይ የሰው ኃይሉን ለማሟሟላት ታቅዷል፡፡የመ/ቤቱ አላማ አስፈፃሚ ሶስት ዳይሬክቶሬቶች ማለትም የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ዳይሬክቶሬት፣የክዋኔና አከባቢ ጥበቃ ኦዲት ዳይሬክቶሬት እና የኦዲት ጥራት ማረጋገጥ፣ትምህርና ሥልጠና ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ስድስቱ ዳይሬክቶሬቶች ደጋፍ ሲሆኑ መ/ቤቱ ከተሠጠው ሥልጣንና ተግባር አንፃር እየተሠሩ ያለው ሥራዎችም የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ እና የአካባቢ ጥበቃ ኦዲት፣ልዩ ኦዲት እና የክልሉ ገ/ኢ/ል/ቢሮ የተጠቃለለ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ፣ለግልና ለማህበራቶች የሂሳብና የኦዲት ሙያ ፈቃድ መስጠት፣የኦዲት ጥራት ማረጋገጥ፣በሂሳብና ኦዲት ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን መሥራት፣ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች፣ ለባለድርሻ አካላት ሙያዊ ድጋፍና ሥልጠና መስጠት ናቸው፡፡በ2017 በጀት ዓመት የ62 መ/ቤቶችን የፋይ/ህ/ኦዲት በማከናወን 73% እንዲሁም የ4 መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት በመሥራት 50% የተደረሰ ሲሆን አጠቃላይ ከዕቅድ አፈፃፀም አኳያ 83% መድረስ የተቻለ ሲሆን የ2018 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ ለመደበኛ እና ለልማት ሥራዎች ማከናወኛ ከተበጀተው በጀት ጋር በማጣጣም ይህ ዝርዝር ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

በቤ/ጉ/ክ/መ/የዋናው ኦዲተር መ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ

1. <u>የዕቅዱ ዋና ዓላማ፣</u>

1.1 የዕቅዱ ዋና ዓላማ በመ/ቤቱ አዋጅ ቁጥር 167/2011 አንቀፅ 6 ሥር የተቀመጡ ዓላማዎችን ከግብ ማድረስ ነዉ፡፡እነሱም፡-

- የክልሉን ዕቅድና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገዉን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ስርዓት መመስረትና ማጠናከር፣
- የክልሉ መንግስት ገንዘብና ንብረት በህግ መሠረት መሰብሰቡን፣መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣ዉጤቱንም ለምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ ፣
- አግባብነት ካላቸዉ አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ዉስጥ በሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲዳብር ጥረት ማድረግ ፣
- የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት የሚደረግበትን ደረጃ ማዉጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል ሲሆን በተጨማሪም የኦዲት ሽፋን እና ጥራት በማሳደግ የደንበኞች እርካታ እንዲጨምር በማድረግ መ/ቤቱ በፍኖተ ብልፅግና ዘመን ዕቅዱ ያስቀመጣቸዉ ራዕይ፣ተልዕኮ፣እሴቶችና በአዋጅ የተሰጠዉን ስልጣንና ተግባራትን በማረጋገጥ በጥረት ተደራሽ ግቦችን ለማሳካት ነዉ፡፡

<u>1.2 ዕቅዱ መነሻ ያደረጋቸዉ ነጥቦች፣</u>

- የመ/ቤቱን የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ፣
- የአምስት ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ ክነውን (ከ2013 እስከ 2017) መነሻ መሰረት በማድረግ፣
- የመ/ቤቱ ቢፒአር ጥናት ሰነድ መሰረት የተፈቀደው ተጨማሪ መደቦች በቂ በጀት ቢፈቀድ ያለውን የሰዉ ኃይል አሁን በስራ ላይ ከሚገኘዉ የተወሰኑ በቅጥር እንደሚጨምር ታሳቢ በማድረግ፣
- በቢኤስስ (BSC) ጥናት ሰነድ የተለዩ ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችን መሠረት በማድረግ በተለዩ አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች እንዲሁም ከተገልጋይና ባለድርሻ አካላት ፍላጎቶች ውስጥ ስትራቴጂያዊ የሆኑ ወሳኝ ጉዳዮችን ትኩረት በመስጠትና መ/ቤቱ በአዋጅ ከተሰጠዉ ሀላፊነት አንፃር ሊያሳካው የሚያስበውን ራዕይና የራዕዩን ውጤት እንዲሁም የተቋሙን ተልዕኮ መነሻ በማድረግ ናቸዉ፡፡

2. የመ/ቤቱ አጠቃላይ ሁኔታ

2.1 የተቋሙ የአሰራር ስርዓት ሁኔታ

የቤ/ጉ/ክ/መንግሥት ዋና ኦዲተር መ/ቤት የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በተገቢዉ ለመወጣት አለም አቀፋዊ /INTO-SAI/፣ አህጉራዊ / AFRO-SAI-E/ የኦዲት ደረጃዎችን በመከተል የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ከፕሪ እንጌጅመንት እስከ ሪፖርት እና የክዋኔ ኦዲትና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት ከአጠቃላይ ዳሰሳ እስከ ክትትል ኦዲት የሚሠራና ሥራዉ በሂደት ላይ እያለ ጥራቱን ለማረጋገጥ የክለሳ፣ የሱፐርቪዥን፣የክትትልና የድጋፍ ሥራዎች በየደረጃዉ በሚገኙት የኦዲት ሥራ አመራሮች የሚሠራ እና የኦዲት ሪፖርቱ ሲጠናቀቅም የኦዲት እስታንዳርዱን አሟልቶ የተሠራ መሆኑን ሥራው ተሠርቶ ከተጠናቀቀ በኃላ የኦዲት ጥራት ሥራ በመ/ቤቱ ውስጥ ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋ ሲሆን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የሚታዩ የአሰራር ግድፈቶችን በማጥናትና ክፍተቶችን በመለየት መፍትሔ በማስቀመጥ፤የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችን የሥጋት ደረጃ በየጊዜው አጥንቶ ማሻሻል፤ በሂሳብ፣ በግዥ፣ በኦዲትና በልዩ ልዩ ሥራዎች ላይ ማነቆ የሆኑትን ችግሮች ለይቶ የማጥናት፣በክልሉ ውስጥ በኦዲት ሙያ ለሚሰማሩ ኦዲተሮችና የሂሣብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ ለኦዲትና የሂሣብ አዋቂዎች በስራው መስክ ለመሠማራት የሚያስችላቸውን የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት መስጠት፣ ማደስ፣ የሙያ ደረጃውን ጠብቀው ማከናወናቸውን መከታተል፣ ሙያዊ ምክር እና ድጋፍ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

2.2 የአመራር ሁኔታ፤

የክልሉን ሀብት አስተዳደር እና አጠቃቀም ውጤታማነትን፣ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ማስፈን እንዲቻል በመ/ቤቱ ውስጥ በየደረጃው ያሉት አመራሮች ቁርጠኛ በመሆን ህግን መሠረት ያደረገ አሠራር በመዘርጋት የመ/ቤቱን ራዕይ ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡

በተጨማሪም በየደረጃው ያሉት የተቋሙ አመራሮች የተቋሙን በጀት፣የሰው ኃይልና ቁሳቁስ በማቀናጀት የሚሠሩ ሥራዎችን እስከ ፈፃሚ በጋራ ተናበው ሪፖርቶችን በማስገምገም የቀጣይ በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች ተነድፏል፡፡በተጨማሪም የተሠሩት ሥራዎች ውጤት ማስገኘቱን በመከታተል ሙያዊ እገዛ በመስጠት፣ በተለይም በኦዲት ሥራ ዙሪያ እንደ ኦዲቱ ጥልቀትና ስፋት፣እንደ ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ ባህሪ አንፃር ለኦዲት ቡድኑ በቦታው በመገኘት የመስክ ሱፐርቪዥን በማድረግ እና ቴክኒካዊ እገዛ በመስጠት፣የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም በመ/ቤቱ በየጊዜው የሚከናወኑ ሥራዎችን ለህብረተሰቡ በማስተዋወቅ፣የ2017 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ በአጠቃላይ በመ/ቤቱ ሠራተኞች በማስገምገም እንዲሁም የ2017 በጀት ዓመት የየሩብ ዓመት ዕቅድ ክንውን ሪፖርት

በየደረጃው ባሉት አመራሮች በማስገምገም በክንውን ጊዜ የታዩ ድክመቶችን እና ጠንካራ ጎኖችን የመለየት ሥራዎች ተሰርቷል፡፡

2.3 <u>የሙያተኞች (ሠራተኞች) ሁኔታ</u>፡- በየደረጃው ያሉት አመራሮች እና ሠራተኞች በ2017 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ እና በ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ ክንውን ላይ በሰፊው የተወያዩ እና ለሠራተኞች 2 (ሁለት) ጊዜ የሥራ ላይ አቅም ግንባታ ሙያዊ ሥልጠናዎች የተሠጣቸው በመሆኑ እያንዳንዱ ሠራተኛ በተመደበበት የሥራ መስክ ጠንክሮ እንዲሠራ ያስችለዋል፡፡በተጨማሪም መ/ቤቱ ሠራተኛው ባለበት ቦታ ሆኖ በቴክኖሎጂ on line ትምህርቱን እንዲከታተል በተለይም የ5 ሚሊዮን የኢ/ያ ኮዲንግ ላይ ገለፃ በማድረግ 21 ሠራተኞች ትምህርት ጀምረው እየተማሩ የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 9 ሠራተኞች የምስክር ወረቀት እንዲሁም መ/ቤቱ ከኢትዮ ቴሌኮም ምዕራብ ምዕራብ ሪጅን አሶሳ ቅርንጫፍ ጋር በመተባበር የፋይዳ መታወቂያ አግኝተዋል፡፡

3. የዕቅድ ዘመኑ የትኩረት መስኮች፡-

3.1 ውጤታማ የኦዲት አገልግሎት

3.2 ስትራቴጂያዊ ትብብርና አጋርነት

4. <u>የመ/ቤቱ ስትራቴጅክ ጉዳዮች</u>

- የኦዲት ሽፋንና ጥራትን ማሳደግ ፣
- የአቅም ውስንነት ያለባቸዉን ሠራተኞች በመለየት የአቅም ግንባታ ስራዎች መስራት፣
- በክልሉ የኦዲትና የሂሳብ ሙያ ፈቃድ አሰጣጥ አጠናክሮ ማስቀጠል፣
- የኦዲት ጥራት ማረጋገጫ ስራ መስራት፣
- ሙያዊ የምክር አገልግሎት መስጠት፣
- ከባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ግንኙነት መፍጠር ፣
- የስጋት ደረጃቸውን በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ መ/ቤቶች ለይቶ በተከታታይ ኢንትሪም ኦዲት ማድረግ፣
- የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮችን መለየትና የኦዲት የትኩረት አካባቢ በማድረግ መስራት፣
- የክትትልና የድጋፍ ስራዎችን ማጠናከር፣
- የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማጠናከር፣
- የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ማጠናከር

5. የመ/ቤቱ ተልዕኮ፣ራዕይ፣እሴቶች፤ኃላፊነትና ተግባር

5.1 የመ/ቤቱ ተልዕኮ /Mission/

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የጥናት ምርምርና የኦዲት እስታንዳርዶችን መሰረት በማድረግ የፋይናንስ ህጋዊነትና የክዋኔ ኦዲት የግንዛቤ ስርፀት የሙያ ምክር አገልግሎት ሥራዎችን ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በመሥራት በክልሉ መንግስትመ/ቤቶች የሀብት አስተዳደርና አሰራር የግልፀኝነትና ተጠያቂነት እንዲጎለብት ማድረግ ነው፡፡

5.2 የመ/ቤቱ ራዕይ /Vision/

በ2022 በኢ/ያ ውስጥ ካሉት ምርጥ የዋናው ኦዲተር መ/ቤቶች አንዱ መሆን፡፡

5.3 የመ/ቤት ዕሴቶች /Core values/

- የሙያ ብቃት/Professionl competence/
- ሚዛናዊነት/Objectivity/
- ቅንነት/Integrity/
- የቡድን ስራ/Team work/
- ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት (Fast & Efficient)

5.4 የመ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

በመ/ቤቱ ተሻሽሎ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 167/2011 በክፍል ሁለት በአንቀፅ 8 መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡

1. መ/ቤቱ በህግ የተሰጠዉን ተግባር ለማከናወን የሚያስፈልገዉ ስልጣን ሁሉ ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን መ/ቤቱ፡-

ሀ/ የክልሉን መንግስት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤

ለ/ ለክልሉ መንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችንና ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፡፡

ሐ/ የክልሉ መንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ህጉን የተከተለ፤ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑንና ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ የክዋኔና የአከባቢ ጥበቃ ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፡፡

መ/ በክልሉ ውስጥ የመረጃ ኦዲት ያደርጋል ያስደርጋል፡፡

ሠ/ የክልሉ መንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች አጠቃላይ የቁጥጥር ስርዓት በበቂ ሁኔታ መነደፉንና በትክክለኛ መንገድና በብቃት ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የሀብት ቁጥጥር ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፡፡

ረ/ በመደበኛ ኦዲት ወቅት የአሰራር ግድፈት ወይም ጉድለት ከመገኘቱ የተነሣ አንድ ሂሣብ በልዩ ሁኔታ ኦዲት እንዲደረግ በምክር ቤቱ፤ በክልል ፍ/ቤቶች እና በሌሎች የመንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች አማካኝነት የተጠየቀ እንደሆነ በጉዳዩ ክብደት ላይ ተመስርቶ የእቅዱ አካል በማድረግ ልዩ ኦዲት ያደርጋል፡፡

ሰ/ ከዚህ በላይ በሠፈሩ ድንጋጌዎች መሰረት ያከናወነውን የኦዲት ሥራ ውጤት ሪፖርት አግባብ ላለው የመንግስት መ/ቤት ወይም ለድርጅት የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡

ሸ/ የኦዲት ውጤቱ ከፍተኛ ጉድለት መከሰቱንና ወንጀል መፈፀሙን የሚያሣይ ሆኖ ሲገኝ ይህንኑ ለክልሉ ፍትህ ቢሮ፣ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤትና ለሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ይልካል፡

ቀ/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች እንዲሁም ከፌደራልና ከክልል ኦዲት መ/ቤቶች ጋር በመመካከር የኦዲት ደረጃ /ስታንዳርድ/ የአሰራር መወሠኛ መመሪያዎች ያወጣል፣

በ/ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለውስጥ ኦዲተሮች ተገቢውን ስልጠናና የሙያ ምክር ይሰጣል፣ እንደአስፈላጊነቱም የውስጥ ኦዲት ሪፖርት እንዲቀርብለት ሊያደርግ ይችላል፡፡

ተ/ አንድ ሂሣብ ወንጀል ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጐደለው አኳኋን መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ ይህንን ሂሣብ የሚመለከቱ ጹሁፎችን፣ መዘክሮችን፣ መዝገቦችን፣ ሰነዶችንና ከነዚህ ጋር ግንኙነት ባላቸው ሌሎች መረጃዎች ላይ በማሸግና በመመርመር ውጤቱን ለሚመለከተው ያሳውቃል

ቸ/ የክልሉ መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የገንዘብና ንብረት ሂሣብ አያያዝና አጠባበቅ አስመልክቶ በሚያዘጋጀው ማንኛውም ህጎች፡ደንቦችና መመሪያዎች ረቂቅ ሥራ ላይ አስፈላጊውን ምክርና አስተያየት ይሰጣል፣

ኀ/ ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግስታት መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሣብና የኦዲት ሙያ ትክክለኛ ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደረጋል፡፡

ነ/ በክልሉ ውስጥ በኦዲት ሙያ ለሚሰማሩ ኦዲተሮችና የሂሣብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ ለኦዲትና የሂሣብ አዋቂዎች በስራው መስክ ለማሠማራት የሚያስችላቸውን የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሣል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል የሙያ ደረጃውን ጠብቀው ማከናወናቸውን ይከታተላል፡ ስልጠናና ምክር ይሰጣል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በህግ አግባብ ክስ ይመሰርታል፡፡

ኘ/ የግል ኦዲተሮችንና የሂሣብ አያያዝ ባለሙያዎችን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት ፣ ለማገድና ለመሠረዝ የሚያስችልና ወጥነት ያለው መመሪያ ያወጣል፡፡

አ/ የምስክር ወረቀቶችን በሚሰጥበትና በሚያድስበት ጊዜ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰነውን የአገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፡፡

ከ/ ኃላፊነቱን በተሟላ ሁኔታ ለመወጣት ይቻለው ዘንድ መጽሐፎችን፡ መዘክሮችን፡ መዝገቦችን፡ ሠነዶችንና ሌሎች መረጃዎችን ለመመልከትና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከህዝብ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት መረጃዎችን ዘገባዎችንና ትንተናዎችን ጠይቆ መቀበል ይችላል፡፡

ኸ/ የመ/ቤቱ ኦዲተሮች ሊከተሉት የሚገባውን ዝርዝር የሙያ ሥነ- ምግባር መመሪያ ያዘጋጃል፡፡

6. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች፤ ውጤቶች

6.1 የትኩረት መስኮች፤

ተ.ቁ	ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ	የሚጠበቅ ዉጤት
1.	ውጤታማ የኦዲት አገልግሎት	የሰፈነ የአሠራር ግልፀኝነትና ተጠያቂነት
2.	ስትራቴጂያዊ ትብብርና አጋርነት	የተቀናጀ የኦዲት አገልግሎት

7. የመ/ቤቱ ስትራቴጅያዊ ዕይታዎች

1. ተገልጋይ
2. የፋይናንስ /በጀት/ ዕይታ
3. የውስጥ አሠራር ዕይታ
4. የመማማርና የዕድገት ዕይታ

8. የመ/ቤቱ ስትራቴጅያዊ ግቦች

ስትራቴጂያዊግብ 1፡- የደንበኞችን እርካታ ማሳደግ፤

ስትራቴጂያዊግብ 2፡- የሀብት ግኝትና የአጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ፣

ስትራቴጂያዊግብ 3፡- የኦዲት አገልግሎትን ማሳደግ፣

ስትራቴጂያዊግብ 4፡- የኦዲት ጥራትን ማሳደግ

ስትራቴጂያዊግብ 5፡- ቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማነትን ማሳደግ፣

ስትራቴጂያዊግብ 6፡- የክትትል ኦዲትን ማጠናከር፣

ስትራቴጂያዊግብ 7፡- ጥናትና ምርምር ስራዎችን ማሳደግ፣

ስትራቴጂያዊግብ 8፡- የአመራርና የሰራተኞች አቅምማሳደግ፣

ስትራቴጂያዊግብ 9፡- ተቋማዊ አሰራርን ማሻሻል፣

ስትራቴጂያዊግብ 10፡- የመረጃ አያያዝና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማጎልበት፣

9. የግቦች መግለጫ (Indicators and scope)

ተ.ቁ	ስትራቴጂያዊ ግቦች	ክብደት (በ%)		የግቡ መግለጫ	ከግብየሚጠበቅውጤት
		የግ/ክ	እይ		
1	የተገልጋይ ዕርካታን ማሳደግ	20	20%	መ/ቤቱ በሚሰጠው አገልግሎት ከተቋቋመለት ዓላማ አኳያ በግልፀኝነት፣ ተአማኒና የተቀላጠፈ የኦዲት አገልግሎት ሰጥቶ የደንበኞችን እርካታ ከማረጋገጡም በላይ የአገልግሎቱ ፈላጊና ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ባገኙት አገልግሎት የእርካታ ደረጃቸውን ከፍ በማድረግ፣ ተገልጋዩን ስለ አገልግሎት አሰጣጥ በማወያዬት፣ ግብረ መልስ በማሰባሰብ ተዓማኒነት ያላቸው በፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት፣ በክዋኔና አከባቢ ጥበቃ ኦዲት ፣ በልዩ ኦዲት ፣ ለግል ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች፣ መ/ቤቱ በሚያደርጋቸው ጥናት እና ምርምር ሥራዎች እንዲሁም ለውስጥ ተገልጋይ የአገልግሎት አሠጣጣችን ላይ የተቀላጠፈና ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት እርካታ መጨመርን ያካትታል፡፡	❖ እርካታዉ ያደገ ተገልጋይ ❖ የተሻሻለ የግልፅኝነትና የተጠያቂነት አሠራር
2	የሃብት ግኝትና የአጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ	15	15%	የመ/ቤቱን አሰራር ውጤታማና ስኬታማ በማድረግ የኦዲት ስራውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ከመንግስት ግምጃ ቤት ለመ/ቤቱ የሚመደብ የመደበኛ እና ካፒታል በጀት፣ከሌሎች አጋር የልማት ድርጅቶች እንዲሁም ከፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የሚገኘውን ሀብት አጠቃቀም ከዕቅድ ጋር አጣጥሞ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ለማስተዳደር የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓትን በመከተል ለታለመለት ዓላማ ላይ ማዋልን ያጠቃልላል፡፡	❖ ያደገ የበጀት አጠቃቀም፣ ❖ ጥራት ያለው ፣ ወቅቱን የጠበቀ የግዥ ስርዓት ይፈጠራል፣ ❖ የታቀዱ ዕቅዶች አተገባበር ደረጃ ይጨምራል፣ ❖ የተቀናጀ እና ግልጽኝነት የሰፈነበት የበጀትና ንብረት አጠቃቀም ይሰፍናል፣ያደገ የበጀት ምንጭ
3	የኦዲትአገልግሎትንማሳደግ፤	18	40%	በክልሉ ከሚገኙ ኦዲት ተደራጊ የመንግስት መ/ቤቶች የኦዲት ሽፋን ለማሳደግ ለሁሉም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔና አከባቢ ጥበቃ ኦዲት አገልግሎት መስጠት፣የኦዲት እና የሂሳብ ሙያ ፈቃድን በመስጠት አስተማማኝና ውጤታማ የሆነ የኦዲት አገልግሎት መስጠትን ያጠቃልላል፡፤	ያደገ የፋ/ህ/ኦዲት እና የክዋኔና አከባቢ ጥበቃኦዲት ሽፋን፣የተሻሻለ የግልፅኝነትና የተጠያቂነት አሠራር ❖ የጎለበተ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ መረጃ አያያዝ፣
4	የኦዲትጥራትንማሳደግ	6		የኦዲት እስታንዳርዱን ሊያሟላ የሚችል የኦዲት ሥራው ተሠርቶ ካለቀ በኃላ የጥራት ደረጃውን የማረጋገጥ ሥራ እና የኦዲት ሥራው በመሰራት ላይ እያለ የሱፐርቭዥን ሥራን በመሥራት የኦዲት ጥራት ቁጥጥር በማረጋገጥ የድጋፍ ሥራዎች የሚሠሩበት ግብ ነው፡፡	❖ በስታንደርድ መሠረት የተከለሰ የኦዲት ዉጤት፣ ❖ በኦዲት ዉጤት ላይ እርካታ ያገኙ ደንበኞች፣ ❖ ያደገና ጥራት ያለዉ በገለልተኛ አካል የተረጋገጠ የኦዲት ዉጤት
5	ቅንጅታዊአሠራርንውጤታማነትማሳደግ፣	4		መ/ቤታችን ለውሳኔ ሰጭ ባለድርሻ አካላት እና ለተገልጋዮች ከሚሰጠው ሙያዊ የምክር አገልግሎት ጎን ለጎን የኦዲት ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ ከፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት፣ ከአቻ የክልል ዋና የኦዲት መ/ቤቶችና በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ባለድርሻ፣ ተገልጋዮችና የኦዲት	❖ በኦዲትና በሂሳብ ሙያ ተቀምሮ የተስፋፋ ተሞክሮ ❖ ያደገ የኮሚንኬሽን ሥራዎች

				አስመላሽ ኮሚቴዎች ጋር በመቀናጀትና በመደጋገፍ፣ ምርጥ ተሞክሮን የመለየት፣የመቀመርና በማስፋፋት አንድ ወጥ የሆነ ግንዛቤ በመያዝ ያልተሸራረፈ የኦዲት ስታንዳርድ ህጎችና የሥራ ማስፈፀሚያ ማንዋሎችን በመጠቀም እንዲሁም የህዝብ ግንኙነት ሥራዎችን በመሥራት የኦዲት አገልግሎትን ማሳለጥና ውጤታማ ማድረግን ያጠቃልላል።	
6	የክትትልኦዲትንማጠናከር	6		ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኦዲት ተደርጎ በሚሠጣቸው የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት እንዲሁም የክዋኔና አክ/ጥ/ኦዲት አስተያየት ሪፖርት መሰረት በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ መውሰዳቸውን ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት ለማድረግ ያለመ ግብ ነው።	❖ ያደገ የኦዲት ምላሽ ሰጪ መ/ቤቶች፣ ❖ ያደገ የግልፀኝነትና ተጠያቂነት አሰራር ፣ ❖ በኦዲት ዉጤት ላይ እርምጃ አወሳሰድ መሻሻል
7	የጥናትናምርምርሥራዎችንማሳደግ	6		ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችን የሥጋት ደረጃ በየጊዜው አጥንቶ ማሻሻል፤በሂሳብ፣በግዥ፣ በኦዲትና በልዩ ልዩ ሥራዎች ላይ ማነቆ የሆኑትን ችግሮች ለይቶ በማጥናት ለሥራው ቀጣይ ማሻሻያ መፍትሔ ማስቀመጥ እንዲሁም በግል ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶችን ማድረግን ያጠቃልላል።	❖ ጥናት ላይ መሠረት አድርጎ የሚሰሩ ሥራዎች ይጨምራሉ፣ጥቅል ተቋማዊ አፈፃፀም ይሻሻላል፣ ❖ ያደገ ጥናትና ምርምር ሥራዎች ዉጤት፣ ❖ ያደገ የማስፈጸም አቅም፣
8	የአመራር እና የሰራተኞችን አቅም ማሳደግ	6	25	ተልዕኮ ተኮር የሆኑና ብቃት ያላቸው መሪዎችን በማበራከት፣ ውጤትን ከአፈጻጸም ባህሪ ጋር በማስተሳሰር ቀጣይነት ያለው የማብቃት ሥራ ማከናወንና የማስፈጸም አቅም መገንባትን ይመለከታል። በየደረጃው የሚገኙ የመ/ቤቱ አመራሮች የመሪነት ሚናቸዉን ስነ-ምግባራዊ እንዲሁም ግልፀኝነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት መልኩ እንዲወጡ የሚያስችላቸዉን የክህሎት ክፍተታቸዉን በመለየት የአጭር፣የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ትምህርት እንዲያገኙ በማድረግ የመደገፍ ሥርዓት የመዘርጋትንና መተግበርን ያካትታል።	❖ የተሰጠዉን ተልዕኮ በብቃት መፈጸም የሚችል አመራር እና ሠራተኞችን ይፈጥራል፣ ❖ የመ/ቤቱ አመራር እና ሠራተኞች ሥራን በተነሳሽነት፣ በቁርጠኝነትና በኃላፊነት ስሜት መወጣት የሚያስችል ሁኔታ ይፈጥራል፣
9	ተቋማዊ አሰራርን ማሻሻል	13		የመ/ቤታችን አገልግሎት ተደራሽነት ለማሳደግ፣ የአስፈጻሚዎችንና የፈጻሚዎችን መዋቅራዊ አደረጃጀት መመሪያዎችን ማሻሻልና አጠቃላይ የህግ ማዕቀፎችና የኦዲት ማኑዋሎችን፣የመ/ቤቱን ዕቅድ እና ሪፖርት በማዘጋጀት እና በመገምገም የትኩረት አቅጣጫን በማስቀመጥ፣ በተቋሙ መዋቅሮች ውስጥ ተገቢነትና ብቃት ባላቸው ሰራተኞች የማሟላትን፣በባለብዙ ዘርፍ ላይ የሚከናወኑ ተግባራትን ታሳቢ ያደረገ ግብ ነው።	• የተሻሻሉ የህግ ማዕቀፎች • ብቃት ያለዉ አደረጃጀት ይፈጠራል፣ • ያደገ የባለብዙ ዘርፍ ተሳትፎ
10	የመረጃ አያያዝ ና ቴክኖሎጅ አጠቃቀም ማጎልበት	6		የመ/ቤቱን የመረጃ አያያዝ ውጤታማ በማድረግ በአንድ ማዕከል በማሰባሰብና በማጠናቀር፤ በሶፍትና ሀርድ ኮፒ በማደራጀት፤እንድጠበቅ በማድረግና ለተገልጋዮች ጠቃሚ መረጃዎችን የመስጠት፤እንዲሁም ለጥናትና ምርምር ስራዎች በግብዓትነት መጠቀም፤የመ/ቤታችን አገልግሎት አሰጣጥ ስኬታማ የሚያደረግ የሰራተኛውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሻሻል በማልማት በመቅዳትና በማላመድ ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ታሳቢ ያደረገ ግብ ነው።	❖ ጠንካራ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት፣ ❖ የተገነባ የቴክኖሎጂ አቅም፣ ❖ ወቅታዊ የመረጃ ልዉዉጥ፣

10. በዕቅድ አፈፃፀሙ የባለደርሻ አካላት

<u>የክልል ም/ቤት፡-</u>

- ሊያሰራ የሚችል የተቋሙ መዋቅር እና የሠራተኞችን ጥቅማ ጥቅም ማስከበር፣
- በመ/ቤቱ የሚቀርቡ ረቂቅ ደንቦች እንዲጸድቁ ማድረግ፣
- በዕቅድ አፈጻጸምሪፖርት ላይ ወቅታዊ ግብረ-መልስ መስጠት፣
- መ/ቤቱ በሚያቀርባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ ፣ የክትትል እና የድጋፍ ሥራ መሥራት ፣

<u>መስተዳደር ም/ቤት</u>

- በመ/ቤቱ ለሚጠየቀው ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፣
- አዲት ተደራጊ መ/ቤት ግዴታቸውን እንዲወጡ በኦዲት ግኝት ላይ ወቅታዊ የእርምት እርምጃና የአስራር ማስተካክያ እንዲወሰድ ማድረግ ፣

<u>ፋይናንስ ቢሮ</u>

- በክልሉ የሚወጡትን ደንብና መመሪያዎች በማሳወቅ፣የመንግስት መ/ቤቶችን የገንዘብ ፍሰትና የንብረት አስተዳደር በመቆጣጠር የውስጥ ኦዲተሮችንና የሂሳብ ባለሙያዎችን በስልጠና አቅማቸውን ማጎልበት፣የተፈቀደውን በጀት በወቅቱ መልቀቅና ዝውውር ማድረግ ፣

<u>ፕላን ልማት ኮሚሽን</u>

- የዕቅድ አፈፃፃም ሪፖርት ግብረ-መልስ መስጠት
- የተሻሻሉ የዕቅድ እና የሪፖርት አሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት

የፌደራል እና አቻ ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች

- የተሻሻሉ የአዲት ማዋሎችን ፣በእርዳታ የሚገኙ ቁሳቁሶችን ፣ተሽከርካሪዎችን፣የበጀት የስልጠና ድጋፎችን በማድረግ ክልላዊ የኦዲት ሽፋንና ጥራት እንዲጎልብት ማድረግ፡፡

በቤ/ጉ/ክ/መ/የዋናው ኦዲተር መ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ

11. የባለፈው በጀት ዓመት የግቦች አፈፃፀም ሁኔታ

ስትራቴጅክ ግብ 1፡- የደንበኞችን እርካታ ማሳደግ

መ/ቤቱ በሚሰጠው አገልግሎት ከተቋቋመለት ዓላማ አኳያ በግልፀኝነት፣ ተአማኒነት ያለው እና የተቀላጠፈ የኦዲት አገልግሎት ሰጥቶ የደንበኞችን እርካታ ከማረጋገጡም በላይ የአገልግሎቱ ፈላጊና ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ባገኙት አገልግሎት የእርካታ ደረጃቸውን ከፍ በማድረግ፣ ተገልጋዩን ስለ አገልግሎት አሰጣጥ በማወያዬት፣ ግብረ መልስ በማሰባሰብ ተዓማኒነት ያላቸው በፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት፣ በክዋኔና አከባቢ ጥበቃ ኦዲት፣ በልዩ ኦዲት፣ለግል ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች የአገልግሎት አሠጣጣችንን፣ መ/ቤቱ በሚያደርጋቸው ጥናት እና ምርምር ሥራዎች እንዲሁም ለውስጥ ተገልጋይ የአገልግሎት አሠጣጣችን ላይ የተቀላጠፈና ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት እርካታ መጨመርን ያካትታል፡፡በዚህ ግብ ስር 1 (አንድ) ግብ ተኮር ተግባር ያለ ሲሆን አፈጻጸሙም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ግብ ተኮር ተግባር1፡-የተገልጋይ እርካታን ማሻሻል የሚያስችሉ መሰረታዊ ጉዳዮችን በትኩረት መስራት

በዚህ በጀት ዓመት የተገልጋዮችንና የባለድርሻ አካላቶችን እርካታ ከ85% ወደ 86% ለማድረስ ታቅዶ 74% ለመድረስ ተችሏል፡፡ይኸውም በተለይ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችን እርካታ ለማወቅ የሰማኒያ አምስት (85) መ/ቤቶች የፋይናንሻል ህጋዊነት እና የስምንት (8) ክ/አከ/ጥ/ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ የስልሳ ሁለት (62) መ/ቤቶች የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት እና የአራት (4) መ/ቤቶች ክዋኔና አከባቢ ጥበቃ ኦዲት ሥራቸው በተጠናቀቁና ክትትል በተደረጉ በኦዲት ዉጤታቸዉ ላይ የመዉጫና የኦዲት መግቢያ ስብሰባ በተደረጉበት ወቅት የማኔጅመንት እርካታ ለማወቅ ከተበተኑ የእርካታ ማረጋገጫ መጠይቆችና ከተሰበሰቡ የተለያዩ አስተያዬቶች እንዲሁም አገልግሎት ለማግኘት ወደ መ/ቤቱ የሚመጡ ተገልጋዮችን እርካታ ለማወቅ የዕለት ከዕለት መከታተያ የአስተያየት መስጫ መዝገብ እና ቅፃ ቅፆች ላይ የሚሠጡት አስተያዬቶችን በመለካት 86% ለመድረስ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የስትራቴጅክ ግብ አፈፃፀም 86% ማሳካት የተቻለ ሲሆን የአፈፃፀም ደረጃው ከፍተኛ ነው፡፡

ስትራቴጅክ ግብ 2፡- የሀብት ግኝትና የአጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ፣

የመ/ቤቱን አሰራር ውጤታማና ስኬታማ በማድረግ የኦዲት ስራውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ከመንግስት ግምጃ ቤት ለመ/ቤቱ የሚመደብ የመደበኛ እና ካፒታል በጀት፣ከሌሎች አጋር የልማት ድርጅቶች እንዲሁም ከፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የሚገኘውን ሀብት አጠቃቀም ከዕቅድ ጋር

አጣጥሞ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ለማስተዳደር የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓትን በመከተል ለታለመለት ዓላማ ላይ ማዋልን የሚያጠቃልል ግብ ነው፡፡በዚህ በጀት ዓመት በዚህ ግብ ስር 4 (አራት) ግብ ተኮር ተግባራት ያሉ ሲሆን ዝርዝር አፈጻጸማቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 1፦የበጀት አጠቃቀምን ማሻሻል

- በዚህ በጀት ዓመት 100% በጀትና ዕቅድን በማጣጣም ሥራ ላይ ለማዋል ታቅዶ 92% ተከናውኗል፣፡ ይኸውም በዚህ በጀት ዓመት መ/ቤቱ የተፈቀደለትን በጀት ከዕቅድ ጋር በማጣጣም የተሻለ የበጀት አጠቃቀም እንዲኖር ለማስቻል የተፈቀደው ውስን በጀት በአግባቡና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን ወቅታዊ የሂሳብ ምዝገባዎች በማከናወን፣ለመ/ቤቱ ሰራተኞች ደመወዝና መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ጥቅማጥቅም በመክፈል፣የመንግስት ደንብና መመሪያን ተከትሎ መለስተኛ የተሸከረካር ጥገናዎች ተከናውኗል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 2፦ከክልሉ መንግስትና ከሌሎች የልማት አጋር ድርጅቶች የተገኘ የፋይናንስ ድጋፍ

- በበጀት ዓመቱ አጠቃላይ ለመ/ቤቱ ከክልሉ መንግስት ለደመወዝ እና ሥራ ማስከጃ የተፈቀደው የመደበኛ በጀት ብር18,607,855.23 ፣ ለኦዲት አገልግሎት 4,100,000 ፣ለቁሳቁስ ግዥ 2,000,000 ሲሆን ሥራ ላይ የዋለው በጀት ደመወዝ እና ሥራ ማስከጃ 18*,607,855.23 አፈፃፀም 100%፣የኦዲት አገልግሎት 4*,100,000 አፈፃፀም 100%፣ለቁሳቁስ ግዥ 2,000,000 አፈፃፀም 99% መድረስ ተችሏል፡፡በአጠቃላይ ለመ/ቤቱ የተበጀተ በጀት 24,707,855.23 ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው 24,707,855.23 በመሆኑ የዚህ ግብ ተኮር ተግባር አፈፃፀም 100 % ለመድረስ ተችሏል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 3፦- ቁጥጥር የተደረገ ሀብት /የፋይናንስና ንብረት/

- ለመ/ቤቱ የሚመደበውን የሀብት ቁጥጥር ከ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት ከ93% ወደ 94% ለማድረስ ታቅዶ 80% ተከናውኗል፡፡ይኸውም በዚህ በጀት ዓመት ከግዥ ን/አስ/ዳይሬክቶሬት በሚመጡ የግዥ እና የጥገና ኘርፎርማዎች ላይ 3 (ሶስት) ጊዜ ቁጥጥር ተደርጓል፣ የመ/ቤቱ ወርሃዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ 12 (አሥራ ሁለት) ጊዜ ተደርጓል፣ የተገዙት አላቂ እና ቋሚ ንብረቶች ገቢ እና ወጪ ሆነው ለሚመለከታቸው ሠራተኞች ፍትሀዊ ክፍፍል የተደረገ ሲሆን አፈፀፃሙም 85% ለመድረስ ተችሏል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 4፡- የግዥ ስርዓትን ማዘመኛ ስራዎችን መስራት

- በዚህ በጀት ዓመት ጥራቱን የጠበቀ የአላቂ እና ቋሚ ዕቃዎች ግዥ በየሩብ ዓመቱ ማለትም 4 (አራት) ጊዜ ለመፈፀም ታቅዶ 3 (ሶስት) ጊዜ ወቅታዊ የሆነ የገበያ ጥናት በማድረግ ለመ/ቤቱ አገልግሎት የሚውሉ አላቂ ዕቃዎች እና የተወሰኑ ቋሚ ዕቃዎች ግዥ በማከናወን አፈፀፃሙም 75% ለመድረስ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የስትራቴጅክ ግብ አፈፃፀም 88% ማሳካት የተቻለ ሲሆን የአፈፃፀም ደረጃው ከፍተኛ ነው፡፡

ስትራቴጅክ ግብ 3፡-የኦዲት አገልግሎትን ማሳደግ

- በክልሉ ከሚገኙ 145 (አንድ መቶ አርባ አምስት) ኦዲት ተደራጊ የመንግስት መ/ቤቶች የኦዲት ሽፋንና ተደራሽነቱን ለማሳደግ ለሁሉም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔና አከባቢ ጥበቃ ኦዲት አገልግሎት ማካሄድ፣የኦዲት እና የሂሳብ ሙያ ፈቃድን መስጠት፣ የባለድርሻ፣ ተባባሪ አካላት፣የህዝብ ክንፍና የውስጥ ኦዲተሮች ሥልጠናዎችን እንድያገኙ የማድረግን አስተማማኝና ውጤታማ የሆነ የኦዲት አገልግሎት መስጠትን ያጠቃልላል፡፡በዚህ በጀት ዓመት በግቡ ስር 7 (ሰባት) ግብ ተኮር ተግባራት የታቀዱ ሲሆን አፈፃማቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 1፡- የተቋማትን ክዋኔና አከባቢ ጥበቃ ኦዲት ማካሄድ

በዚህ በጀት ዓመት 8 (የስምንት) መ/ቤቶችን የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ 4 (የአራት) መ/ቤቶች ማለትም 1 (አንድ) ከፍተኛ ፣1 (አንድ) መካከለኛ እና 2 (ሁለት) አነስተኛ የሥጋት ደረጃ የተፈረጁ መ/ቤቶች የኦዲት ሥራቸዉ የተጠናቀቁ በመሆኑ አፈፃፀም 50% ለመድረስ ተችሏል፡፡የመ/ቤቶቹ ዝርዝር ገጽ 18 ላይ ይመልከቱ፡፡

የአፈፃፀም ደረጃው ዝቅ ያለበት ምክንያት፡- ነባር ቡድን መሪዎች ማለትም አራት ቡድን መሪዎች የተሻለ ደመወዝና ጥቅማጥቅም ፍለጋ መ/ቤቱን በመልቀቃቸው የተነሣ አዲስ ቡድን መሪዎች ለሥራው አዲስ በመሆናቸው ፤ በዚህም ምክንያት አሁን ስራ ላይ የሚገኙ አብዛኛዉ ኦዲተሮች ከፍተኛ የልምድ ማነስ እና የሙያ ሥልጠና አለማግኘት፣ በስትራቴጅክ መሪው ዕቅድ ላይ ይሟላል ተብሎ የታቀደው የሰው ኃይል /ባለሙያ/ አለመሟላት የዕቅድ ክንዉን አፈጻጸሙ በታቀደው ልክ እንዳይፈፀም አድርጎታል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 2፣ የፋይናንሻልና ህጋዊነት ኦዲት ማካሄድ፣

በዚህ በጀት ዓመት 85 (ሰማንያ አምስት) የፋ/ህ/ኦዲት መ/ቤቶችን ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ የ62 (የስልሳ ሁለት) መ/ቤቶችን ማለትም 8 (ስምንት) በጣም ከፍተኛ ስጋት ደረጃ፣ 10 (አሥር) ከፍተኛ ስጋት ደረጃ፣11 (አሥራ አንድ) መካከለኛ ስጋት ደረጃ፣ 4 (አራት) አነስተኛ ስጋት ደረጃ እና 29 (ሃያ ዘጠኝ) በጣም አነስተኛ ስጋት ደረጃ የተፈረጁ መ/ቤቶች በድምሩ 62 (የስልሣ ሁለት) መ/ቤቶች የኦዲት ሥራቸው ሙሉ በሙሉ ኢንተሪም ኦዲት እና በመደበኛ ሙሉ በጀት ዓመት የተጠናቀቁ በመሆናቸው አፈፃፀም 73% ለመድረስ ተችሏል፡፡የመ/ቤቶቹ ዝርዝር ከገጽ 18 (አሥራ ስምንት) እስከ 23 (ሃያ ሶስት) ላይ ይመልከቱ፡፡

- **የዕቅድ አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት :-**
  1) ከፍተኛ የኦዲት ሥራ ልምድ ያካበቱ (ያላቸው)የቡድን መሪዎች እና ኦዲተሮች የተሻለ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ፍለጋ ተቋሙን በመልቀቃቸው፣
  2) የኦዲት ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በተለይ ላኘቶፕ ኮምፒዩተር እስከ ሶስተኛ ሩብ ዓመት ድረስ ያልተሟላ በመሆኑ አሁንም በሚፈለገው ልክ አለመሟላቱ፣
  3) የኦዲት ሥራን ለመሥራት በ24ቱ (በሃያ አራቱ) ወረዳዎች እና በክልል ተቋማት ካሉት መ/ቤቶች ኦዲት ለማድረግ ቢታቀድም የኦዲት ሥራችን በአሶሳ ከተማ ውስጥ ብቻ በከፊል የተወሰኑ ተቋማት መተከል ዞን ብቻ ላይ በመሠራቱ፣
  4) አሁን ሥራ ላይ የሚገኙ የኦዲት መስክ ቡድን መሪዎች እና ኦዲተሮች 70% በላይ በኦዲት ሥራ የልምድ ማነስ ያለባቸው እና አዳዲስ በመሆናቸው፣
  5) በኦዲት ሥራ የሱፐርቭዥን ሥራ በሚፈለገው መጠን ለመሥራት እንዲቻል እና ኦዲተሮችን ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር የተሽከሪካር እጥረት በመኖሩ ምክንያት በኦዲት ሥራ ጊዜ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ በመፍጠሩ የኦዲት ሥራ አፈፃፀማችንን ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 3፣ከበጀት አንፃር የኦዲት ሽፋን ማሳደግ ፣

- በዚህ ግብ ተኮር ተግባር ውስጥ 2 (ሁለት) ተግባራት ያሉ ሲሆን የመጀመሪያው ተግባር ከሌላ አካል በቀረበዉ ጥያቄ መነሻነት ልዩ ኦዲት የተደረገ በጀትን ሳይጨምር የኦዲት ሽፋንን

በአጠቃላይ በ2016 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት ፀድቆ በሥራ ላይ ከዋለ በጀት ዉስጥ 86%ቱን በኦዲት ለመሸፈን ታቅዶ 60%ቱን በኦዲት ለመሸፈን የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 70% ለመድረስ ተችሏል፡፡

- በዚህ በጀት ዓመት መስፈርቱን አሟልው ለሚመጡ ለግል ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች የሙያ ፈቃድ ሴርቲፍኬት ለ2 (ሁለት) ለመስጠት ታቅዶ 2 (ሁለት) ተመዝጋቢዎች ፈተና ተሰቷቸዉ የተሰጣቸውን ፈተና በማለፋቸው ለ2ቱም የሙያ ሰርትፍኬት በመሰጠቱ ክንውን 100% ለመድረስ ተችሏል፡፡በተጨማሪም መስፈርቱን አሟልቶ ለሚመጡ 14 (ለአሥራ አራት) የግል ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች የሙያ ፈቃድ ለማሳደስ ታቅዶ 14 (ለአሥራ አራቱም) ፈቃዳቸው የታደሰ በመሆኑ ክንውን 100% ለመድረስ ተችሏል፡፡

<u>ግብ ተኮር ተግባር 4</u>፡-የፀደቁ የኦዲት ሪፖርቶች በመቶኛ፣

- በዚህ ግብ ተኮር ተግባር ውስጥ 2 (ሁለት) ተግባራት ያሉ ሲሆን የመጀመሪያው ተግባር የኦዲት ስራቸዉ አልቆ የመዉጫ ስብሰባ የተደረጉ 62 (ስልሣ ሁለት) የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት እና 4 (አራት) መ/ቤት የክዋኔ ኦዲት በመ/ቤታችን በማቋቋሚያ አዋጅ ላይ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ መሰረት ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ግብረ-መልስ ቀርቦ አስተያየት ተሰቷቸዉ በመ/ቤታችን ኃላፊዎች የፀደቁ ሪፖርቶችን እንዲሁም 5 (የአምስት) ልዩ ኦዲት መ/ቤት ሪፖርትን ጨምሮ በሙሉ አፅድቆ ለሚመለከታቸዉ አካላት ለማስተላለፍ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ሁሉንም የኦዲት ሪፖርቶች ለሚመለከታቸዉ አካላት በማስተላለፍ አፈፃፀም 100% ለመድረስ ተችሏል፡፡
- ሁለተኛው ተግባር ለጉባኤ የሚቀርብ የተጠቃለለ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ እና አከባቢ ጥበቃ ኦዲት ሪፖርት ለማቅረብ ታቅዶ ሪፖርቱ የተዘጋጀ በመሆኑ አፈፃፀም 100% ለመድረስ ተችሏል፡፡

<u>ግብ ተኮር ተግባር 5</u>፡-የኦዲት ሥራቸው የተጠናቀቁ መ/ቤቶች ሪፖርት ላይ የመውጫ ውይይት ማካሄድ፣

- በዚህ በጀት ዓመት የኦዲት ሥራቸዉ የተጠናቀቁ በሙሉ መ/ቤቶች ኦዲት ዉጤት ላይ ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የማኔጅመንት አባላት ጋር የመዉጫ ዉይይት ለማድረግ ታቅዶ በ62 (በስልሣ ሁለት) የፋይናንስና ህጋዊነት እንዲሁም በ4 (በአራት) የክዋኔ ኦዲት መ/ቤት የኦዲት ውጤት ላይ የመውጫ ስብሰባ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ለመድረስ ተችሏል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 6፡-ምላሽ ያገኙ የልዩ የኦዲት አገልግሎት ጥያቄዎች በመቶኛ

በዚህ በጀት ዓመት ከተለያዩ አካላት ቀርበው የሚመዘገቡትንና የመ/ቤታችንን የማቋቋሚያ አዋጅ የማይቃረኑትን የልዩ ኦዲት ጥያቄዎችን 7 (ሰባት) ተጠይቆ ከዚህ ውስጥ የ5 (የአምስት) መ/ቤቶች ልዩ ኦዲት የተጠናቀቀ በመሆኑ አፈጻፀም 71% ለመድረስ የተቻለ ሲሆን ቀሪው 2ቱ (ሁለቱ) መ/ቤቶች በሂደት ላይ ናቸው፡፡ዝርዝር መ/ቤቶቹ ገጽ ከ23 (ሃያ ሶስት) እስከ 24 (ሃያ አራት) ላይ ይመልከቱ፡፡

<u>ግብ ተኮር ተግባር 7፡-</u> ለግል ሂሳብ አዋቂዎች እና ኦዲተሮች፣ ለተገልጋይ፣ ለባለድርሻ አካላት እና ለውስጥ ኦዲተሮች ተከታታይነት ያለውን ስልጠና መስጠት

በዚህ በጀት ዓመት በቁጥር 160 (አንድ መቶ ስልሣ) ለሚሆኑ ሠልጣኞች ማለትም ለግል ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች፣ለተገልጋዮች እና ለባለድርሻ አካላት ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ 84 (ሰማኒያ አራት) ለሚሆኑ የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች በመ/ቤታችን አዋጅ ጋር ተያይዞ ከኦዲት ተደራጊ ጋር ያለንንነ ግንኙነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና የተሰጣቸው በመሆኑ አፈፃፀም 53% ለመድረስ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ስትራቴጅክ ግብ አፈፃፀም 77% ለማድረስ የተቻለ ሲሆን ደረጃውም መካከለኛ ነው፡፡

ስትራቴጅክ ግብ 4፡-የኦዲት ጥራትን ማሳደግ

- የኦዲት ደረጃዎችን (Standards) ሊያሟላ የሚችል የኦዲት ሥራው ተሠርቶ ካለቀ በኃላ የጥራት ደረጃውን የማረጋገጥ ሥራ እና የኦዲት ሥራው በመሰራት ላይ እያለ የሱፐርቭዥን ሥራን በመሥራት የኦዲት ጥራት ቁጥጥር በማረጋገጥ የድጋፍ ሥራዎች የሚሠሩበት ግብ ነው፡፡ በግቡ ስር 3 (ሶስት) ግብ ተኮር ተግባራት የታቀዱ ሲሆን አፈፃማቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 1፡-በኦዲት ሥራ ዙሪያ የሱፐርቪዥን ስራ ማካሄድ

የኦዲት ጥራትን ለማስጠበቅ በዕቅድ በተያዙ የመደበኛ እና የክትትል ኦዲት መ/ቤቶችን የኦዲት ሥራቸዉ የተጠናቀቁ 62 (የስልሣ ሁለት) የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት መ/ቤቶች፣4 (አራት) የክዋኔና አከባቢ ጥበቃ ኦዲት መ/ቤት እና 5 (አምስት) የልዩ ኦዲት መ/ቤት እንዲሁም የኦዲት ሥራቸዉ ተጀምሮ በመከናወን ላይ የሚገኙ መ/ቤቶችን ጨምሮ በተቀመጠዉ የጥራት ስታንዳርድ መሰረት የሱፐርቪዥን ስራ 100% ለማድረስ ታቅዶ 100% የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ለመድረስ ተችሏል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 2፡-በግል ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ዙሪያ የሱፐርቭዥን ሥራ ማካሄድ

በዚህ በጀት ዓመት 24 (ለሃያ አራት) ተፈቀደላቸው የሂሳብ አዋቂዎች የሱፐርቪዥን ሥራ ለመስራት ታቅዶ 15 (ለአስራ አምስት) የግል ሂሳብ ሙያ ፈቃድ ወስደው እየሠሩ ላሉት ባለሙያዎች የሱፐርቪዥን ሥራ የተሠራ ሲሆን አንድ የተፈቀደለት የሂሳብ አዋቂ መ/ቤቱ ያወጣውን ደንብ ተላልፎ በመገኘቱ የታገደ እና 8ቱ (ስምንት) የግል ሂሳብ አዋቂዎች ሙያ ፈቃድ ወስደው በሥራ ላይ የለሉ ሲሆን ለ15ቱ (ለአሥራ አምስቱ) የሱፐርቪዥን ሥራ ግብረ-መልስ የተሠጠ በመሆኑ አፈፃፀም ከ100% ለማከናወን ተችሏል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 3፡- የኦዲት ጥራት መስፈርቶችን ተከትሎ መሥራት

በዚህ በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የስራ ወረቀቶችንና ሪፓርቶችን በተቀመጠላቸው የኦዲት ደረጃዎች መሰረት የተከናወነ መሆኑን 85% የኦዲት ጥራት የማረጋገጥ ስራ ለመስራት ታቅዶ 70% ተከናውኗል፡፡ ይኸውም የድባጤ ወረዳ እና የቡለን ወረዳ ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት የ2016 በጀት ዓመት የስራ ወረቀት የጥራት ማረጋገጥ ስራው የተከናወነ በመሆኑ አፈፃፀም 82% ለመድረስ ተችሏል፡፡
በአጠቃላይ ስትራቴጅክ ግብ አፈፃፀም 94% ለማድረስ የተቻለ ሲሆን ደረጃውም በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

ስትራቴጅክ ግብ 5፡- ቅንጅታዊ አሠራርን ውጤታማነት ማሳደግ

መ/ቤታችን ለውሳኔ ሰጭ ባለድርሻ አካላት እና ለተገልጋዮች ከሚሰጠው ሙያዊ የምክር አገልግሎት ጎን ለጎን የኦዲት ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ ከፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት፣ ከአቻ የክልል ዋና የኦዲት መ/ቤቶችና በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ባለድርሻ፣ተገልጋዮችና የኦዲት አስመላሽ ኮሚቴዎች ጋር በመቀናጀትና በመደጋገፍ፣ ምርጥ ተሞክሮን የመለየት፣የመቀመርና በማስፋፋት አንድ ወጥ የሆነ ግንዛቤ በመያዝ ያልተሸራረፈ የኦዲት ስታንዳርድ ህጎችና የሥራ ማስፈፀሚያ ማንዋሎችን በመጠቀም የኦዲት አገልግሎትን አሰጣጥ ውጤታማ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡በዚህ ግብ ውስጥ 2 (ሁለት) ግብ ተኮር ተግባራት የታቀዱ ሲሆን አፈፃፀማቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 1፡- የምክክር መድረክ ማዘጋጀት

በዚህ በጀት ዓመት 2 (ሁለት) ጊዜ የኦዲትና የሂሳብ ሙያ እንዲዳብር የምክከር መድረክ ለመሳተፍ ታቅዶ ማለትም ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ ከደቡብ፣ ከሲዳማ እና ከማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች እንዲሁም ከድሬ-ደዋ እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ጋር የጋራ የምክክር መድረክ በድሬ-ዳዋ ከተማ እና በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአርባ- ምንጭ ከተማ የተካሄደ በመሆኑ አፈፃፀሙም 100% ለመድረስ ተችሏል፡፡

ዝርዝር ተግባር 1፡- የኦዲትና የሂሳብ ሙያ እንዲዳብር የተደረገ የልምድ ልውውጥ

በዚህ በጀት ዓመት 1 (አንድ) ጊዜ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከአቻ ክልሎች በማምጣት እና በመቀመር ወደ ኦዲተሮች ለማውረድ ታቅዶ ከክልሎች እና ከከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት ጋር በተደረገዉ ልምድ ልዉዉጥ ተሞክሮዎች የተገኘ በመሆኑ አፈፃፀም 100% ለመድረስ ተችሏል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 2፡- በኦዲት አገልግሎት ዙሪያ የኮሚንኬሽን *ሥራዎችን መሥራት*

በዚህ በጀት ዓመት በኦዲት አገልግሎት ዙሪያ 100% የህዝብ ግንኙነት *ሥራዎች* ውጤታማነት ለማሳደግ ታቅዶ በመ/ቤቱ የተሠሩትን ወቅታዊ መረጃዎች ለተገልጋዮች እና ለባለድርሻ አካላት በክልሉ ሚዲያ ዜና እንዲተላለፍ ተደርጓል፣*በኦዲት ግኝት የመውጫ ስብሰባ ላይ በመገኘትና በመዘገብ እንዲሁም የመ/ቤቱን አጠቃላይ ሥራዎች በመ/ቤቱ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ በየወቅቱ በመልቀቅ መረጃውን ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን በመደረጉ አፈፃፀም* 100% ለማከናወን ተችሏል፡፡

አጠቃላይ የስትራቴጂክ ግብ አፈፃፀም 100% ማሳካት የተቻለ ሲሆን የአፈፃፀም ደረጃው በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

ስትራቴጅክ ግብ 6፡-የክትትል ኦዲትን ማጠናከር

ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኦዲት ተደርገው በሚሠጣቸው የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት እንዲሁም የክዋኔና አክ/ጥ/ኦዲት አስተያየት ሪፖርት መሰረት በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ መውሰዳቸውን ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት ለማድረግ ያለመ ግብ ነው፡፡ በግቡ ውስጥ 2 (ሁለት) ግብ ተኮር ተግባር የታቀደ ሲሆን አፈፃፀሙም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ግብ ተኮር ተግባር 1፡- የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በፋይናንሻልና ህጋዊነት ኦዲት ዉጤትና አስተያዩት መሰረት እርምጃ መዉሰዳቸዉን የክትትል ኦዲት ማድረግ

- በዚህ በጀት ዓመት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኦዲት ተደርገው በሚሰጣቸዉ የፋይናሻል ህጋዊነት የኦዲት አስተያዬት መሰረት በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ መዉሰዳቸዉን በ80 (በሰማኒያ) መ/ቤቶች ላይ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ61 (በስልሣ አንድ) መ/ቤቶች ላይ ክትትል የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙም 76% ለመድረስ ተችሏል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 2፡- የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት ዉጤትና አስተያዩት መሰረት እርምጃ መዉሰዳቸዉን የክትትል ኦዲት ማድረግ

በዚህ በጀት ዓመት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኦዲት ተደርጎ በሚሰጣቸዉ የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ የኦዲት አስተያየት ሪፖርት መሰረት በወቅቱ ማናጅመንቱ የማስተካከያ እርምጃ መዉሰዱን በ4 (በአራት) መ/ቤቶች ላይ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ1 (በአንድ) መ/ቤት ላይ ክትትል የተደረገ ሲሆን አፈፃፀም 25% ለመድረስ ተችሏል፡፡አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት የነባሪ ቡድን መሪዎች በአንድ ጊዜ መልቀቅ **/አራት ቡድን መሪዎች/** የተነሳ በቦታቸዉ በአዲስ ቡድን መሪዎች ማደራጀት እና ለሥራዉ አዲስ

መሆን፣በአሁኑ ወቅት በሥራ ክፍል ሥር ያሉ ኦዲተሮች ለሥራዉ ልምድ ማነስ እና የሙያ ስልጠና አለማግኘት ፣በስትራቴጂክ መሪ ዕቅድ /የ10 እና የ5 ዓመት ዕቅድ/ ይሟላል ተብሎ የታቀደዉ የሰዉ ሀይል /ባለሙያ/ አለመሟላት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ስትራቴጅክ ግብ አፈፃፀም 51% ማሳካት የተቻለ ሲሆን የአፈፃፀም ደረጃው ዝቅተኛ ነው፡፡

ስትራቴጂክ ግብ፡- 7 የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማሳደግ

ከመ/ቤቱ ፖሊሲና ስትራቴጂ ዕቅድ፤ ከዓለም አቀፍና አገር አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች በመነሳትና የመ/ቤቱን የኦዲት ጥራት ደረጃ ማጥናት፤በመ/ቤታችንም ሆነ በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የሚታዩ የአሰራር ግድፈቶችና የሥጋት ደረጃዎችን በማጥናት ክፍተቶችን በመለየት መፍትሔ ማስቀመጥ፤ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችን የሥጋት ደረጃ በየጊዜው አጥንቶ ማሻሻል፤በሂሳብ፣በግዥ፣በኦዲትና በልዩ ልዩ ሥራዎች ላይ ማነቆ የሆኑትን ችግሮች ለይቶ በማጥናት ለሥራው ቀጣይ ማሻሻያ መፍትሔ ማስቀመጥ እና ሌሎች የኦዲት ሽፋን፣ጥራት፣ ክትትል ድጋፍ እና ግንዛቤ የማጎልበት ስራዎች፣የሂሳብ አዋቂዎች ፍቃድ አሰጣጥና ጥናትን መሰረት ባደረገ ሁኔታ መስራትን ያጠቃልላል፡፡በዚህ ግብ ውስጥ 1 (አንድ) ግብ ተኮር ተግባር የታቀደ ሲሆን አፈፃፀሙም እንደሚከተለው ቀርባል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 1፡-በግል ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ዙሪያ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት

በዚህ በጀት ዓመት 1 (አንድ) ጊዜ በግል ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ ባለመከናወኑ አፈፃፀም 0% ለመድረስ ተችሏል፡፡ያልተከናወነበት ምክንያት በዘርፉ የሰው ኃይል አለመሟላት

ስትራቴጂክ ግብ አፈፃፀም 0% ሲሆን የአፈፃፀም ደረጃው በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

<u>ስትራቴጂክ ግብ- 8፡-</u> የአመራር እና የሰራተኞችን አቅም ማሳደግ

ተልዕኮ ተኮር የሆኑና ብቃት ያላቸው መሪዎችን በማበራከት፣ ውጤትን ከአፈጻጸም ባህሪ ጋር በማስተሳሰር ቀጣይነት ያለው የማብቃት ሥራ ማከናወንና የማስፈጸም አቅም መገንባትን ይመለከታል፡፡ በየደረጃው የሚገኙ የመ/ቤቱ አመራሮች የመሪነት ሚናቸዉን ስነ-ምግባራዊ እንዲሁም ግልፀኝነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት መልኩ እንዲወጡ የሚያስችላቸዉን የክህሎት ክፍተታቸዉን በመለየት የአጭር፣የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ትምህርትና ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ የማድረግን፣ በየደረጃ የሚገኙ ፈጻሚና አስፈፃሚ አመራር አካላትን፣ የመደገፍ ሥርዓት የመዘርጋትንና መተግበርን

ያካትታል፡፡በዚህ በጀት ዓመት በዚህ ግብ ስር 2 (ሁለት) ግብ ተኮር ተግባር የታቀደ ሲሆን አፈፃሙም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 1፡-<u>ለአመራሮች እና ለሠራተኞች የአጫጭር ጊዜ ሥልጠና ማመቻቸት</u>

በ2017 በጀት ዓመት በመ/ቤቱ በመፈጸም አቅም ክፍተት ላይ የተመሠረተ የአጫጭር ጊዜ ሥልጠናዎች የሚያስፈልጋቸውን ለ50% ማለትም ለ48ቱ (ለአርባ ስምንቱ) የመ/ቤቱ አመራሮች እና ሠራተኞች በመለየት አቅማቸው እንዲጎለብት የአጫጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን ለመሥጠት ታቅዶ ለ95 (ለዘጠና አምስት) ለመ/ቤቱ በየደረጃው ላሉት አመራሮች እና ሠራተኞች ማለትም 55 (ሃምሳ አምስት) ወንድ እና 40 (አርባ) ሴት በጥንድ ሂሳብ አያያዝ፣ በግንባታ ሂሳብ ኦዲት እና በFAM የሥራ ወረቀት ላይ ስልጠና የተሰጠ በመሆኑ አፈፃፀም ከ100% በላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር፡- 2 <u>የትምህርት ዕድል ያገኙ አመራርና ሠራተኞች በቁጥር</u>

በዚህ በጀት ዓመት ለ2 (ለሁለት) የመ/ቤቱ ሠራተኞች የረጅም ጊዜ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ1 (ለአንድ) ሰራተኛ የረጅም ጊዜ የትምህርት ዕድል እንዲያገኝ የተደረገ በመሆኑ አፈፃፀም 50% ለመድረስ ተችሏል፡፡፡

ስትራቴጂክ ግብ አፈፃፀም 75% ማሳካት የተቻለ ሲሆን የአፈፃፀም ደረጃው መካከለኛ ነው፡፡

ስትራቴጅክ ግብ 9፡- ተቋማዊ አሠራርን ማሻሻል

የመ/ቤታችን አገልግሎት ተደራሽነት ለማሳደግ፣ የአስፈጻሚዎችንና የፈጻሚዎችን መዋቅራዊ አደረጃጀት መመሪያዎችን ማሻሻልና አጠቃላይ የህግ ማዕቀፎችና ማኑዋሎችን፣የስራ ዕቅዶችን ማዘጋጀት፣መከለስና በተቋሙ መዋቅሮች ውስጥ ተገቢነት ያላቸውና ብቃት ባላቸው ሰራተኞች የማሟላትን፣የባለብዙ ዘርፍ ተሳትፎን በማሳደግ ለተቋሙ ተልዕኮ ስኬት በጋራ መቆምን የሚያመላክት የአሰራር ህጎችና መመሪያዎች ማንዋል ማጥናት እና ማሻሻል የሚል ግብ ሲሆን በዚህ ግብ ስር 4 (አራት) ግብ ተኮር ተግባራት ታቅዷል፡፡

ግብ ተኮር 1፡-የአሰራር ህጎች፣ ደንቦች፤ መመሪያዎችና ማንዋሎች ማጥናትና ማሻሻል ፡-

በዚህ በጀት ዓመት 1 (አንድ) ጊዜ የአሰራር ህጎች፣ ደንቦች፤መመሪያዎችና ማንዋሎችን አጥንቶ ለማሻሻል ታቅዶ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ጥቅማጥቅም እና መተዳደሪያ ደንብ የተዘጋጀ በመሆኑ አፈፃፀም 100% ለመድረስ ተችሏል፡፡

ግብ ተኮር 2፡-የመ/ቤቱን የሰው ኃይል ማሟላት፤- በዚህ በጀት ዓመት የመ/ቤቱ ተቋማዊ አደረጃጀትና አሰራር ለማጠናከር በመ/ቤቱ ካሉት ክፍት መደቦች ውስጥ 10 የሥራ መደቦችን ለመሸፈን ታቅዶ አራት የስራ መደብ በሰው ኃይል ለመሸፈን የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 40% ለመድረስ ተችሏል ፡፡አፈፃፀም ዝቅ ያለበት ምክንያት መ/ቤቱ ከሚፈፅመው የሥራ ክብደት አንፃር ተመጣጣኝ ክፍያ ባለመኖሩ፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 3፡-የመ/ቤቱን እቅድና ክንዉን በወቅቱ መገምገምና የትኩረት አቅጣጫ ማስቀመጥ

በዚህ በጀት ዓመት የመ/ቤቱን ሰራተኞች እና በደረጃው ያሉትን አመራሮች ያሳተፈ 5 (አምሰት) ጊዜ የዕቅድና የሪፖርት ግምገማ ለማድረግ ታቅዶ አምስት ጊዜ ተከናውኗል፡፡ይኸውም የመ/ቤቱን የ2016 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ ክንውን፣የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ፣የ2017 በጀት የ1ኛ፣ የ2ኛ፣ የ3ኛ እና የ4ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ ክንውን በየደረጃው ባሉት አመራሮች በመገምገም እና የቀጣይ ጊዜያቶች የትኩረት አቅጣጫዎች እንዲቀመጡ በማድረግ አፈፃፀሙም 100% ለመድረስ ተችሏል፡፡

ግብ ተኮር 4፡-ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን ማከናወን

በዚህ በጀት ዓመት ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን 2 (ሁለት) ጊዜ ለማከናወን ታቅዶ መ/ቤቱ ከክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ጋር በመፃፃፍ ወላጅ ያጡ እና ተጋላጭ ለሆኑት ለ4 (ለአራት) ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ማለትም ዩኒፎርም፣ደብተር፣እስክርብቶ እና ቦርሳ ተገዝቶ ተሰጧቸዋል፣ ከሠራተኞች ደመወዝ የሚቆረጠውን ወርሃዊ የኤድስ ፈንድ ለአራቱም ህፃናት በየወሩ ለእያንዳንዳቸው አምስት መቶ ብር ወርሃዊ ክፍያ እንዲያገኙ በማድረግ አፈፃፀሙም 100% ለመድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በየዓመቱ ህዳር 22 ቀን የሚከበረውን የዓለም አቀፍ የኤች.አይ.ቭ ቀንን እና የካቲት 29 ቀን ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን አስመልክቶ አጠቃላይ ከመ/ቤቱ ሠራተኞች ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ስትራቴጅክ ግብ አፈፃፀም 88% ማሳካት የተቻለ ሲሆን የአፈፃፀም ደረጃው ከፍተኛ ነው፡፡

ግብ 10. የመረጃ አያያዝና ቴክኖሎጅ አጠቃቀምን ማጎልበት

የመ/ቤቱን የመረጃ አያያዝ ውጤታማ በማድረግ በአንድ ማዕከል በማሰባሰብና በማጠናቀር፤በሶፍትና ሀርድ ኮፒ በማደራጀት፤እንድጠበቅ በማድረግና ለተገልጋዮች ጠቃሚ መረጃዎችን የመስጠት፤እንዲሁም ለጥናትና ምርምር ስራዎች በግብዓትነት መጠቀም፤የመ/ቤታችን አገልግሎት አሰጣጥ ስኬታማ የሚያደረግ የሰራተኛውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሻሻል በማልማት በመቅዳትና በማላመድ ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ታሳቢ ያደረገ ግብ ሲሆን በግቡ ስር 2 (ሁለት) ግብ ተኮር ተግባራት የታቀዱ ሲሆን አፈፃፀማቸውም እንደሚከተው ቀርቧል፡፡

በቤ/ጉ/ክ/መ/የዋናው ኦዲተር መ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ

ግብ ተኮር ተግባር 1፡-የተሻሻለ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ አጠቃቀም

በዚህ በጀት ዓመት የተሻሻለ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ አጠቃቀም ከ85% ወደ 86% ለማድረስ ታቅዶ 80% ለመድረስ ተችሏል፡፡ ይኸውም ዘመኑ ባፈራቸው ቴክኖሎጂዎች በመታገዝ የኦዲት ሪፖርቶችን የመላላክ፣የድጋፍና ክትትል ስራዎች በመስራት ፣የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወይም በኮምፒውተር ዕውቀት በመታገዝ ከአይቤክስ ላይ ለኦዲት ሥራ የሚያግዙትን መረጃዎችን በመውሰድ የኦዲት ስራን በተቀላጠፈ ሁኔታ በመስራት WhatsApp, E-mail, Portal One Office አገልግሎት ለመጀመር ቅድመ ሁኔታዎች በመጠናቀቃቸው አፈፃፀም 93% ለመድረስ ተችሏል፡፡

ግብ ተኮር ተግባር 2፡-በኢፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ታግዞ የተደራጀ መረጃ

በዚህ በጀት ዓመት 100% አጠቃላይ መ/ቤቱ ኦዲት አድርጎ የኦዲት ስራቸው የተጠናቀቁ የኦዲት ስራ ወረቀትና ሪፖርቶችን ሙሉ በሙሉ መረጃዎችን ለማደራጀት ታቅዶ የኦዲት ሥራ ወረቀቶችና ሪፖርቶችን በሀርድ እና በሶፍት ኮፒ መረጃዎች ተደራጅተው የማስቀመጥ ሥራ ተሠርቷል፡፡በተጨማሪም ሁሉም ዳይሬክቶሬቶች የዳይሬክቶሬቶቻቸውን መረጃዎች ሙሉ በሙሉ በሀርድ እና በሶፍት ኮፒ አደራጅቶ የማስቀመጥ ሥራ ለማከናወን የተቻለ በመሆኑ አፈፃፀም 90% ለመድረስ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የስትራቴጂክ ግብ አፈፃፀም 97% ማሳካት የተቻለ ሲሆን የአፈፃፀም ደረጃው በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

12. የመ/ቤቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

- የተገልጋይ እና የባለድርሻ አካላት የእርካታ ደረጃቸውን ከፍ ማድረግ፣
- የመ/ቤቱ የበጀት አጠቃቀም የተሻለ እንዲሆን መስራት፣
- የኦዲት አገልግሎት ሽፋን እንዲያድግ በትኩረት መስራት፣
- ቅንጅታዊ አሰራር ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣
- የኦዲትና ሂሳብ ሙያ ፍቃድ ፈላጊዎች አስፈላጊዉን የሙያ ሰርቲፊኬት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በግል ኦዲትና ሂሳብ አዋቂዎች የሚሰሩ ስራዎች ጥራታቸዉን እንዲጠብቁ የቁጥጥርና ድጋፍ ስራን መስራት፣
- በመ/ቤቱ የኦዲት ስታንዳርድ መሰረት የኦዲት ጥራት ማረጋገጥ ስራን በትኩረት መስራት፣
- የኦዲት ግኝት እርምጃ አወሳሰድን በተመለከተ የክትትል ኦዲት ስራን አጠናክሮ መስራት፣
- ልዩ-ልዩ የጥናትና ምርምር ስራዎችን መስራት፣
- ለአመራሮች፤ለሠራተኞች እና ለባለድርሻ አካላት ስልጠና በመስጠት በኦዲት ዙሪያ ግንዛቤ የማሳድግ ስራን መስራት፣

- በመ/ቤቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እንዲያድግ በትኩረት መስራት፣

13.የማስፈጸሚያ ስልቶች

የታቀደውን ዕቅድ ስኬታማ ለማድረግ የሚረዱን የማስፈጸሚያ ስልቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡-

- የመ/ቤቱን አደረጃጀት በሰው ኃይል እና በሎጅስትክ በማጠናከር፣
- በየደረጃው ያሉትን አመራር እና ባለሙያ ሥራውን በባለቤትነትና በተነሳሽነት እንዲመሩ በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት ከመቼውም በበለጠ ወቅታዊ ስልጠና በመስጠት የአፈፃፀም አቅማቸውን በማሳደግ፣
- ከክልሉ መንግሥት እና ከለጋሽ ድርጅቶች የሚገኘውን በጀትና ድጋፍ ማሳደግና በቁጠባ በመጠቀም፣
- ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል አሰራር በመንደፍ፣
- በግልና በማህበር ለሚደደራጁ የሂሳብ እና ለኦዲት ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ በመስጠት እና አስፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ፣
- የመ/ቤቱ ሠራተኞች በመልካም ሥነ-ምግባር እንዲታነፁ እና የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ በሥርዓተ-ፆታ ላይ ፣ በኤች.አይ.ቪ. መከላከል ላይ ፣ በመልካም ሥነ ምግባር ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር፣
- የመረጃ አሰባሰብ እና አያያዝ የሚያስችል የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት፤
- ለኦዲት ሥራ አጋዥ የሆኑ የጥናት እና የምርምር ሥራዎችን በማጠናከር

14. የ2018 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ ዝርዝር

ተ.ቁ	ስትራቴጂያዊ ግብ፤ግብ ተኮር ተግባራትና ዝርዝር ተግባራት	ግብ ክብደት	መለኪ ያ	መነሻ አፈፃፀም (የ2017ዓ.ም.)	የዕቅድ ዓመቱ ኢላማ (የ2018ዓ.ም.)	የዕቅድ አመቱ ሩብ ዓመት ኢላማ				ማስፈፀሚያ በጀት
						1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	
1	**ስትራቴጂያዊ ግብ 1፡-የደንበኞችን እርካታ ማሳደግ**	20								
1.1	**ግብ ተኮር ተግባር 1**									
	የተገልጋይ እርካታን ማሻሻል የሚያስችሉ መሰረታዊ ጉዳዮችን በትኩረት መስራት	20	በመቶኛ	74%	88%	77%	80%	84%	88%	
2	**ስትራቴጂያዊ ግብ 2፡-**የሀብት ግኝትና የአጠቃቀምን ውጤታማነትን ማሳደግ	15								
2.1	**ግብ ተኮር ተግባር 1**									
	በጀትና ዕቅድን በማጣጣምሥራ ላይ ማዋል	3	በመቶኛ	92%	100%	100%	100%	100%	100%	
2.2	**ግብ ተኮር ተግባር 2**									
	ከክልሉ መንግስትና ከሌሎች የልማት አጋር ድርጅቶች የተገኘ የፋይናንስ ድጋፍ በብር (000)	4	በብር	24,707.8	30.989.9					
2.3	**ግብ ተኮር ተግባር 3**									
	ሀብትን በዕቅድና በቁጠባ መጠቀም	3	በጊዜ	80%	12	3	6	9	12	
2.4	**ግብ ተኮር ተግባር 4**									
	የግዥ ስርዓትን ማዘመን	3	በጊዜ	3	4	1	2	3	4	
	ስትራቴጂያዊ ግብ ፡-3 የኦዲት አገልግሎትን ማሳደግ	18								
3.1	**ግብ ተኮር ተግባር 1**									
	የተቋማትን የክዋኔ ኦዲት ማካሄድ	3	በቁጥር	4	6	-	3	-	6	
3.2	**ግብ ተኮር ተግባር 2**									
	የተቋማትን የፋይናንሻልና ህጋዊነት ኦዲት ማካሄድ	5	በቁጥር	62	86	10	35	50	86	
3.3.1	**ዝርዝር ተግባር 1**									
	ለግል ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች የሙያ ፈቃድ መስጠት	1	በቁጥር	2	3	1	2		3	
3.3.2	**ዝርዝር ተግባር ፡ 2**									
	ለግል ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች የሙያ ፍቃድ ማደስ	1	በመቶኛ	14	15	10	12		15	
3.4	**ግብ ተኮር ተግባር 4**									
	የኦዲት ሪፖርት በወቅቱ ፀድቆ እንዲወጣ ማድረግ	2	በቁጥር	71	92	10	38	53	92	

በቤ/ጉ/ክ/መ/የዋናው ኦዲተር መ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ

ተ.ቁ	ስትራቴጂያዊ ግብ፤ግብ ተኮር ተግባራትና ዝርዝር ተግባራት	ግብ ክብደት	መለኪያ	መነሻ አፈፃፀም (የ2017ዓ.ም.)	የዕቅድ ዓመቱ ኢላማ (የ2018ዓ.ም.)	የዕቅድ አመቱ ሩብ ዓመት ኢላማ				ማስፈፀሚያ በጀት
						1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	
3.4.1	**ዝርዝር ተግባር 1**									
	ለጉባኤ የሚቀርብ የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት ማዘጋጀት	1	በቁጥር	2	2	1		2		
3.5	**ግብ ተኮር ተግባር 5**									
	የኦዲት ስራቸዉ የተጠናቀቁ መ/ቤቶች ሪፖርት ላይ ማኔጅመንቱ ጋርየመውጫ ዉይይት ማካሄድ	2	በቁጥር	65	92	10	38	53	92	
3.6	**ግብ ተኮር ተግባር 6**									
	የሚቀርቡ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎችን ለመ/ቤታችን የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር የማይፃረሩ ከሆነ ተቀብሎ ኦዲት ማድረግ	3	በቁጥር	5	7	1	3	5	7	
3.7	**ግብ ተኮር ተግባር 7**									
	ለግል ሂሳብ አዋቂዎች፣ለኦዲተሮች፣ለተገልጋዮች፣ ለባለድርሻ አካላት እና ለውስጥ ኦዲተሮች ተከታታይነት ያለዉ ሥልጠና መስጠት	2	በቁጥር	84	200	50	100	150	200	
4	**ስትራቴጂያዊ ግብ 4** የኦዲት ጥራትን ማሳደግ	6								
4.1	**ግብ ተኮር ተግባር 1**									
	በኦዲት ሥራ ዙሪያ የሱፐርቪዥን ስራ ማካሄድ	2	በቁጥር	71	92	10	38	53	92	
4.2	**ግብ ተኮር ተግባር 2**									
	ሱፐርቭዥን የተደረገባቸው የግል ሂሳብና የኦዲት ሙያ ፈቃድ በቁጥር	2	በቁጥር	15	15	8			15	
4.3	**ግብ ተኮር ተግባር 3**									
	የኦዲት ጥራት መስፈርቶችን ተከትሎ መሥራት	2	በቁጥር	70%	5			2	5	
5	**ስትራሰቴጂያዊ ግብ፤- 5 ቅንጅታዊ አሰራርን ዉጤታማነት ማሳደግ**	4								
5.1	**ግብ ተኮር ተግባር ፡ 1**									
	የምክክር መድረክ ማዘጋጀት	2	በቁጥር	1	1				1	
5.2	**ዝርዝር ግብ ተኮር ተግባር 2**									
	ምርጥ ተሞክሮዎችን ከአቻ ክልሎች በማምጣትና በመቀመር ወደ ስራ ማስገባት	2	በቁጥር	1	2		1		2	

በቤ/ጉ/ክ/መ/የዋናው ኦዲተር መ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ

ተ.ቁ	ስትራቴጂያዊ ግብ፤ግብ ተኮር ተግባራትና ዝርዝር ተግባራት	የግብ ክብደት	መለኪያ	መነሻ አፈፃፀም (የ2017ዓ.ም.)	የዕቅድ ዓመቱ ኢላማ (የ2018 ዓ.ም.)	የዕቅድ አመቱ ሩብ ዓመት ኢላማ				ማስፈፀሚያ በጀት
						1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	
	ግብ ተኮር ተግባር									
	በኦዲት አገልግሎት ዙሪያ የኮሚንኬሽን ሥራዎችን መሥራት	2	በጊዜ	100%	60	15	30	45	60	
6	**ስትራሰቴጂያዊ ግብ፤-6 የክትትል ኦዲት ስራ ማጠናከር**	6								
6.1	**ግብ ተኮር ተግባር 1**									
	የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በፋይናንሻልና ህጋዊነት ኦዲት ዉጤትና አስተያዬት መሰረት እርምጃ መዉሰዳቸዉን የክትትልና የድጋፍ ስራ መስራት	3	በቁጥር	61	86	10	35	50	86	
6.2	**ግብ ተኮር ተግባር 2**									
	የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በክዋኔ ኦዲት ዉጤትና አስተያዬት መሰረት እርምጃ መዉሰዳቸዉን የክትትልና የድጋፍ ስ ራመስራት	3	በቁጥር	1	4	1	2	3	4	
7	**ስትራቴጂያዊ ግብ 7 ፡-የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማሳደግ**	6								
7.1	**ግብ ተኮር ተግባር 1**									
	በተቋማት ላይ የተደረገ የስጋት ደረጃ ክለሣ ጥናት	2	*በቁጥር*		-	-	-	-	1	
7.2	**ግብ ተኮር ተግባር 2**									
	በግል ሂሳብ አዋቅዎችና ኦዲተሮች ዙሪያ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት	2	*በቁጥር*		-	-	-	-	-	
7.3	**ግብ ተኮር ተግባር 3**									
	በሂሳብ፣ በግዥ እና በኦዲት ሥራ ዙሪያ ልዩ ልዩ ጥናታዊ ሥራዎችን መሥራት	2	*በቁጥር*	-	-	-	-	-	-	
8	**ስትራቴጂያዊ ግብ ፡-8 የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ማሳደግ፣**	6								
8.1	**ግብ ተኮር ተግባር 1**									
	ለአመራሮች እና ለሰራተኞች የአጫጭር ጊዜ ሥልጠና ማመቻቸት	3	በመቶኛ	100%	120		60		60	
8.2	**ግብ ተኮር ተግባር 2**									

በቤ/ጉ/ክ/መ/የዋናው ኦዲተር መ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ

ተ.ቁ	ስትራቴጂያዊ ግብ፤ግብ ተኮር ተግባራትና ዝርዝር ተግባራት	የግብ ክብደት	መለኪያ	መነሻ አፈፃፀም (የ2017ዓ.ም.)	የዕቅድ ዓመቱ ኢላማ (የ2018ዓ.ም.)	የዕቅድ አመቱ ሩብ ዓመት ኢላማ				ማስፈፀሚያ በጀት
						1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	
	ለአመራሮች እና ለሠራተኞች የረጅም ጊዜ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ ማመቻቸት	3	በቁጥር	1	1				1	
9	**ስትራሰቴጂያዊ ግብ፤-9 ተቋማዊ አሰራርን ማሻሻል**	13								
9.1	**ግብ ተኮር ተግባር 1**									
	የአሰራር ህጎች፣ ደንቦች፤ መመሪያዎችና ማንዋሎች ማጥናትና ማሻሻል	3	በቁጥር	1	2		1		2	
9.2	**ግብ ተኮር ተግባር 2**									
	ብቁ ሠራተኞችን በመቅጠር የመ/ቤቱን መዋቅር በሰዉ ኃይል ሟሟላት	3	በቁጥር	4	9	2	9			
9.3	**ግብ ተኮር ተግባር 3**	6								
	የመ/ቤቱን ዕቅድ እና ክንውን በወቅቱ በመገምገምና የትኩረት አቅጣጫ ማስቀመጥ		*በቁጥር*	5	5	2	3	4	5	
9.4	**ግብ ተኮር ተግባር 4**	2								
	በሴቶች፣በወጣቶች፣በሥርዓተ-ፆታእኩልነት፣በኤች.አይ.ቨ /ኤዲስ/፣ እና በሥነምግባር ዙሪያ ውይይት ማካሄድ		*በቁጥር*	2	2		1	2		
10	**ስትራቴጂያዊ ግብ፤-10 የመረጃ አያያዝና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማጎልበት**	6								
10.1	**ግብ ተኮር ተግባር 1**									
	የተሻሻለ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በቁጥር	3	በቁጥር	80%	89	50	60	80	89	
10.2	**ግብ ተኮር ተግባር 2**									
	በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ታግዞ የተደራጀ መረጃ	3	በቁጥር	100%	92	10	38	53	92	

በቤ/ጉ/ክ/መ/የዋናው ኦዲተር መ/ቤት የ2018 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ